ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

# ጳጉሜ አንድ ቀን ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን የላቀ አገልግሎት የሰጡ የመንግሥት ሠራተኞች የምስጋና አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 973-/2015

ነሐሴ/2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር 973-2015
## ጳጉሜ አንድ ቀን ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን የላቀ አገልግሎት የሰጡ የመንግሥት የምስጋና አፈፃፀም መመሪያ

በሀገር አቀፍ ደረጃ ጳጉሜ አንድ ቀን የአገልግሎት ቀን ሆኖ እንዲከበር በመንግስት የተወሰነ በመሆኑ በዕለቱ ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ምስጋና ሊቀርብላቸው የሚገቡ ሠራተኞችን ለይቶ ማበረታታት በማስፈለጉ፣

በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የረጅም ጊዜ አገልግሎት በመስጠት ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ላገለገሉ ሠራተኞች ግልጽ በሆነ አሰራር ሥርዓት ዕውቅናና ሽልማት መስጠት በማስፈለጉ፣

በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ (2) በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ጳጉሜ አንድ ቀን ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን የላቀ አገልግሎት የሰጡ መንግሥት ሠራተኞች የምስጋና አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 973/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. "**አዋጅ**" ማለት የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው፡፡
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
   3. "**ደንብ**" ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 502/2014 ነው፡፡
   4. "**ኮሚሽን**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡
   5. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

3. **የጾታ አገላለጽ**

   በዚህ መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   በፌዴራል መንግስት በተመደበ በጀት በሚተዳደሩ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. **የመመሪያው ዓላማ**

   በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት በመጠቀም የረጅም ጊዜ አገልግሎት በመስጠት ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሠራተኞችን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚከበረው የአገልግሎት ቀን ምስጋና ለመስጠት እና

ሌሎች ሠራተኞችም ለማበረታታትና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል የዜጎችን እርካታ ለማሳደግ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የምስጋናና ሽልማት አፈጻጸም

### 6. የሠራተኞች መምረጫ መስፈርት

1. ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ጳጉሜ አንድ ቀን ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን ለምስጋናና ዕውቅና የሚመርጠው ሠራተኛ በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ 38 ዓመትና በላይ ያገለገለ ሰራተኛን ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተመረጠውን ሠራተኛ ግለ ታሪክ ከኮሚሽኑ ለዚህ ተግባር በተላለፈው ደብዳቤ መሠረት መረጃውን በትክክል በመሙላት መላክ አለበት፡፡

### 7. ለሠራተኛው የሚሰጠው ሽልማት

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት ለተመረጠው ሠራተኛ የምስጋና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

2. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ጳጉሜ አንድ ቀን በሚከበረው የአገልግሎት ቀን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሰረት ተመርጦ ዝርዝሩ ለኮሚሽኑ የተላለፈው ሠራተኛ ለወንድ ሠራተኞች ደረጃውን የጠበቀ ሙሉ ልብስ (ሸሚዝና ከረባትን ጨምሮ) እንዲሁም ለሴት ሠራተኞች የሀበሻ ሙሉ ልብስ በመሥሪያ ቤቱ ተገዝቶ ይሰጣል፡፡

3. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ለምስጋናና ሽልማቱ ለተመረጠ ሠራተኛ ከብር 10,000 (አስር ሺህ) እስከ 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) ብር ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

   *ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ህጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡*

9. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

   *ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ ጳጉሜ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ለሚከበረው የአገልግሎት ቀን ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡*

**መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር)**
**የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**
**ኮሚሽነር**